## 1. መግቢያ

የኢቦላ በሽታ ለህመምና ሞት የሚዳርግ በሽታ ቢሆንም ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መከላከል ይቻላል፡፡ በሽታው በተለይ በመካከለኛውና በምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች በተደጋጋሚ በወረርሽኝ መልክ በመከሰት ህመምና ሞት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም በምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች መከሰቱ ታውቋል፡፡ በሀገራችንም በማንኛውም ወቅት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2. የኢቦላ በሽታ ምንድን ነው?

የኢቦላ በሽታ በቫይረስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ሲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ከወዲሁ በማድረግ መከላከል ካልተቻለ በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው በመተላለፍ ለህመም ብሎም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡፡

## 3. የኢቦላ በሽታ እንዴት ይተላለፋል?

የኢቦላ በሽታ በሚከተሉት መንገዶች ይተላለፋል፡፡

- በበሽታው የታመመን ሰው ቁስል፣ ደም፣ ምራቅ፣ ትውከት፣ አይነምድርና ሽንት በቀጥታ በመንካት እንዲሁም ፈሳሾች ወደ አይን ከተረጨና ከገቡ
- ከላይ የተጠቀሱትን በበሽታው የተበከሉ መኝታዎች፣ አልባሳት (አንሶላ፣ ብርድልብስ፣ ወዘተ.) በመንካት፣
- ንጽህናው ያልተረጋገጠ ወይም ሌሎች ህሙማን የተጠቀሙበት መርፌ ሳይቀቅሉ በመጠቀም፣
- የኢቦላ በሽታ ታማሚ የተጠቀመበትን መርፌና ስለት ያላቸውን መሳሪያዎች በመጠቀም፣
- በኢቦላ በሽታ የሞተ ሰውን አስከሬን በቀጥታ በመነካካት፣
- በኢቦላ በሽታ የሞተ እንስሳ ስጋ በመመገብ ናቸው፡፡

## 4. በኢቦላ በሽታ የተያዘ ሰው ምልክቶችን የሚያሳያው መቼ ነው?

በኢቦላ በሽታ ከተጠቃ ሰው ጋር ንክኪ የፈጠረ ሰው ከ 2 እስከ 21 ቀናት ውስጥ የበሽታውን ምልክቶች ማሳየት ይጀምራል፡፡

## 5. በበሽታው የተያዘ ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶችና ስሜቶች

በኢቦላ በሽታ የተጠቃ ሰው

- ከፍተኛ የሆነ ድንገተኛ ትኩሳት፣
- ማስመለስ/ትውከት፣
- ተቅማጥ፣
- ራስ ምታት፣
- በቆዳ ላይ ሽፍታ መታየት እና የዓይን መቅላት፣
- የመድማት ምልክት በሰውነታችን ክፍት ቦታዎች ማለትም አይን፣ አፍንጫ፣ ድድ፣ ጆሮ፣ ፊንጢጣና በብልት በኩል (ይህ አንዳንድ ጊዜ ላይታይም ይችላል)፡፡

## 6. በበሽታው የተያዘ ሰው ከገጠመን ምን ማድረግ አለብን?

- ታማሚውን በምንረዳበት ጊዜ ሰውነታችንን ከበሽታው መከላከል የሚያስችሉንን የእጅ ጓንት፣ የአይን መከላከያ መሳሪያ (ጎግል) እና የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛ ማስክ መጠቀም፣
- የታመመው ሰው ወድያውኑ ለህክምናና እርዳታ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ጤና ተቋም እንዲሄድ ማድረግ፣
- በበሽታው የተጠረጠረ ሰው በሚገኝበት ወቅት ወድያውኑ በአቅራብያው **ወደሚገኘው ጤና** ተቋም ወይም ጤና ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ ፣
- በበሽታው መያዙ የተጠረጠረ ወይም የታመመ ሰው የተጠቀመበትን አልባሳትና መኝታ ለአገልገሎት ከማዋል ወይም ከመጠቀም በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በሚገባ በበረኪና ማጠብ ይኖርብናል፡፡

## 7. ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑት እነማን ናቸው?

- የኢቦላ በሽታ ከታመመ ሰው የሚወጣውን ደምና ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች በቀጥታ በመንካት የሚተላለፍ በመሆኑ ከታመመው ሰው ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው በበሽታ ሊያዝ ይችላል፡፡ በመሆኑም በሽተኛውን በምንመግብበትና በምንንከባከብበት ጊዜ የእጅ ጓንትና ሌሎች መሰሪያዎች አለማድረግ በቀላሉ ለበሽታው እንድንጋለጥ ያደርጋል፡፡
- በኢቦላ በሽታ የሞተን ሰው አስከሬን ያለ እጅ ጓንትና ሌሎች ቀደም ብሎ የተጠቀሱ የመከላከያ መሳሪያዎችን ሳንጠቀም የምነካ ከሆነ በቀላሉ በበሽታው ልንጠቃ እንችላለን፡፡

## 8. በሽታውን እንዴት ልንከላከል እንችላለን?

- በበሽታው ከተጠቃ ሰው የሚወጣውን ማንኛውም ፈሳሽ እንዲሁም ቁስል የእጅ ጓንት፣ የአይን ጎግል እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሳሪያዎችን ሳይጠቀሙ ባለመንካት፣
- በሽታው የተያዘ ሰው የተጠቀመበትን መርፌና ሌሎች ስለት ያለቸው መሳሪያዎች ባለመጠቀም፣
- በበሽታው መያዛቸው የተጠረጠሩ እንዲሁም የሞቱ እንስሳት ስጋን ባለመመገብ፣
- በበሽታው የታመመን ሰው ከረዳን ወይም በኢቦላ በሽታ የሞተን ሰው አስከሬን ከነካን በኋላ እጃችንን በንጹኅ ውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ፣

- በሽታው የሞተን ሰው አስከሬን በምንነካበት ጊዜ ጓንትና ሌሎች የመከላከያ መሰሪያዎችን በመጠቀም  የሰውነት ፈሳሽ ንክኪን በመከላከል እንዲሁም የቀብር ሥነ-ሰርዓትንም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈፀም በማድረግ እንዲሁም ከቀብር በኋላ ያለውን ሥነ-ሰርዓትን በማሳጠር፣
- በአካባቢያችን የበሽታዉ ምልክት ያለበት ሰዉ ከታየ፣ በበሽታዉ መታመሙ የተጠረጠረ ወይም የሞተ ሰው ካለ በአቅራቢያዉ ለሚገኝ ጤና ድርጅት ወይም የአካባቢዉ ጤና ጽ/ቤት **በአስቸኳይ** ሪፖረት በማድረግ  መከላከል ይገባል፡፡

## 9. በቤት ውስጥ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን ለብቻው በተዘጋጀ ቦታ መለየት፣
- በበሽታው የተጠቃን ሰው በምንረዳበት ወይም በምንከባከብበት ጊዜ የእጅ ጓንት፣ የአይን ጎግል፣ የፊት መሸፈኛ እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሳሪያዎች  መጠቀም፣
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን ወደ ጤና ተቋማት በምናጓጉዝበት ጊዜ የተጠቀሱትን መከላከያዎች ሳያደርጉ ታማሚን አለመንካት፣
- በአጋጣሚ በበሽታው የተጠቃን ወይም የተጠረጠረን ሰው ወይም የሰውነት ፈሳሽ ከነኩ ወዲያውኑ በንጹኅህ ውሃና በሳሙና መታጠብ፣
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰው የሰውነት ፈሳሽ መሬት ከበከለ በረኪና መጨመርና ከ15 ደቂቃ በኋላ  ማፅዳት እንዲሁም የተበከሉ ቁሳቁሶችና ልብሶች ካሉ ማቃጠል፣
- በበሽታው ታሞ የሞተ ሰው የቀብር ስነስርዓት ለማከናወን በቅድሚያ መከላከያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም አስከሬኑን በፕላስቲክ ከረጢት መጠቅለል፣ መከላከያ ቁሳቁስ ሳይጠቀሙ በምንም መልኩ አስከሬኑን አለመንካትና የጋራ የእጅ መታጠቢያ አለመጠቀም እንዲሁም የቀብር ስነስርዓቱን በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ምክር በመታገዝ ማከናወን ናቸው፡፡

## 10. የሪፖርት አደራረግ

- ማንኛውም ሰው አጣዳፊ ትኩሳትና ትውከት ካለበት፣ ተቅማጥና የቆዳ ሽፍታና በቀላሉ የመድማት ችግሮች ከታዩበት የኢቦላ በሽታ ታማሚ ነው ተብሎ ሊጠረጠር ይችላል፡፡ ምልክቶቹ እንደታዩ ወዲያዉኑ በላብራቶሪ ተመርምሮ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- አንድ ታማሚ በኢቦላ በሽታ መታመሙ በላብራቶሪ ከተረጋገጠ በሽተኛዉ ባለበት አካባቢ ወረርሽኝ መከሰቱን ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለሚመለከታቸዉ አካላት በአስቸኳይ ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
- ከላይ እንደተጠቀሰው ማንኛውም ሰው ድንገተኛ የሆነና ከፍተኛ ትኩሳት ካለበት የመድማት ችግር ቢኖርም ባይኖርም በአፋጣኝ ወደጤና ድርጅት እንዲሄድ በማድረግ በአካባቢው ለሚገኝ ጤና ድርጅትም ሆነ መንግስታዊ መዋቅር ሪፖርት ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም የሞት ሁኔታ (ከአደጋ በስተቀር) በአካባቢያችን ካለ ወይም መኖሩ ከታወቀ በአቅራቢያዉ ለሚገኝ ጤና ድርጅት ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡


**ለተጨማሪ መረጀ**

**በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

- የጤና ኤክስቴንሽንና መሰረታዊ ጤና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣  የጤና አጠባበቅ ትምህርት ኬዝ ቲም
  ስልክ ፡ +251 11 515 54 25
- የኢትዮጵያየ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
  የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል
  ስልክ፡+251 11 275 8631
  +251 11 276 5340


# ከኢቦላ በሽታ ራስዎን፤ ቤተሰብዎን እና ማሕበረሰብዎን ይከላከሉ!




በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር  የተዘጋጀ

ጳጉሜ2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ